# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፤ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 352 ጥር 29

በአርበኞች ግንቦት 7: እምነት መሠረት የፓሊስ ከፍተኛ አዛዦች ህወሓቶች ቢሆኑም አብዛኛው የሠራዊቱ አባል በህወሓት ዘረኛና ፋሽስታዊ አገዛዝ የተማረረ፤ የሥርዓቱ መለወጥ የሚፈልግና ሥርዓቱን ለመለወጥ የሚደረገውን ትግል የሚደግፍ ኃይል ነው። ስለሆነም ህወሓት የተለየ ጦር አሰልጥኖ የፓሊስ ልብስ በማልበስ ነውረኛ ወንጀል በማሠራት ፓሊስን ለማስጠላት የሚያደርገው ሴራ ሊጋለጥ ይገባል ብሎ ያምናል።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የእንግሊዝ ፓርላማ አባላት በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አስከፊ የመብት ረገጣ ውይይት አደረጉ

የእንግሊዝ የፓርላማ አባላት በመጭው ወር የንቅናቄያችን ዋና ጸሃፊ የአቶ አንዳርጋቸ ጽጌ ጉዳይን በተመለከተ ከጉጅሌው ሹማምንት ጋር ለመምከርና፤ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የሚገኙበትን ሁኔታ በአካል ተገኝተው ለመታዘብ ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ እቅድ መንደፋቸው የተዘገበ ሲሆን ጉዞው ከመካሄዱ በፊት የፓርላማ አባላቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው አጠቃላይ የመብት ረገጣና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሰፊ ውይይት ማካሄዳቸውን ለማወቅ ተችሏል። ባሳለፍነው ጥር 27 2015 ኢ.ም ለንደን ውስጥ በኢትዮጵያ ጉዳይ ዙሪያ ሰፊ ውይይት ያካሄዱት የእንግሊዝ የፓርላማ አባላት በኢትዮጵያ በርካታ ዜጎች ስደትን እንደ አማራጭ የሚጠቀሙት በአገሪቱ ከተንሰራፋው የዲሞክራሲ እጦት የተነሳ ነው ብለዋል። በኢትዮጵያ ስላለው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፤ የነፃ ፕሬስ አፈናና የዲሞክራሲ ግብአቶች መክሰም ዙሪያ ማስረጃዎችን በማጣቀስ የተወያዩት የፓርላማ አባላቱ በመጨረሻ ኢትዮጵያ አሁን ለምትገኝበት ውድቀት የጉጅሌውን አገዛዝና ቱባ ሹማምንቱን ተጠያቂነት አድርገዋል።

## ወያኔ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ መጠቀሚያ ማድረጉን የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችን አስቆጣ

ከ 7 ወራቶች በፊት ከመን ሰንአ አየር ማረፊያ ላይ ታፍነው ለጉጅሌው ወያኔ ተላልፈው የተሰጡት የንቅናቄያችን ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በጠላት እጅ ከወደቁ በኋላ ለ 3 ጊዜያት በአገዛዙ ቴሌቪዥን ቀርበው እንዲናገሩ የተደረጉት በግዳጅ መሆኑን በመጠቆም የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ የግለሰቡን ሰብአዊ መብቶች በመጣስ ለአገዛዙ ርካሽ የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ በሚል እየተደረገ ያለው ፍፁም ህጋዊ ያልሆነ አካሄድ መቆም አለበት ሲሉ ተቀማጭነታቸውን በእንግሊዝ ያደረጉ የተለያዩ የጻረ ግርፋትና የሞት ተሟጋች ተቋማት አስታውቀዋል። ድርጅቶቹ አገዛዙ የለቀቃቸውን የተለያዩ ቪዲዮዎች በደንብ የተመለከቷቸው መሆኑንና ለስነ ልቦና ባለሞያዎች ማስጠናታቸውን የገለጹ ሲሆን አገዛዙ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ ከፍተኛ ሰቆቃና ቶርቸር እየፈጸመባቸው እንደሚገኝ ከስነ ልቦና ባለሞያዎች ባገኙነው መረጃ ለማረጋገጥ መቻላቸውን አመልክተዋል። ድርጅቶቹ አያይዘውም ከቤተሰቦቻቸው፤ ከህግ ባለሞያዎች እንዲሁም አግባብነት ካላቸው አካላት እንዳይገናኙ የታገዱት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ክፉኛ እንዳሳሰባቸው በመግለጽ በጉዳዮ ዙሪያ ለእንግሊዝ መንግስት የተለያዩ ደብዳቤዎችን እንደፃፉ ገልጸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በተመለከተ ባቀረቧቸው ሶስት ተከታታይ ድራማዎች ከፍተኛ ቅሌትና ውርደትን የተከናነበው ዘረኛው የሕወሓት አገዛዝ፤ አሁንም በአቶ አንዳርጋቸው ላይ ርካሽ የፓለቲካ ትርፍ ለማጋበስ በማሰብ ይቅርታ እንዲጠይቁ ለማድረግ እያግባቡቸው እየተማጸኑዋቸው እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ይህን ካደረጉ በሌሉበት የተበየነባቸውን የሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ እስራት ሊያዘዋውሩላቸው እንደሚችሉ እያግባቡቸው እንደሚገኙ ከውስጥ ምንጮቻችን የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

## ዘረኛው ወያኔን ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርጎ ለማዉጣት ሕዝባዊ ትግሉ ተፋፍሞ መቀጠል አለበት

ላለፉት 24 የጨለማ አመታት ኢትዮጵያን በቀኝ ግዛት በመያዝ ህዝቦቿን ለመከራና ለስቃይ የዳረገው ዘረኛው የሕወሓት አገዛዝ ሰሞኑን ምርጫ ቦርድ የተሰኘውን የአገዛዙ ጉዳይ አስፈፃሚ ተቋም ተጠቅሞ ሁለቱን ከፍተኛ ህዝባዊ ድጋፍ ያላቸውን ፓርቲዎች አንድነትና መኢአድን ማፍረሱን እና ህገ ወጥ ለሆኑትና አገዛዙ ለፈጠራቸው ተለጣፊ ቡድኖች በመስጠቱ በኢትዮጵያ ዘንድ ቁጣ መቀስቀሱን መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን የተቆጡት ነፃነት ናፋቂ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በኋላ አገራችንና ህዝባችንን ነፃ ለማውጣት እየተደረገ ባለው ትግል እያንዳንዱ ...... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ታዋቂዉ ጋዜጠኛ ግርሀም ፔብል ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ አገዛዝ ሽብርተኛ ነዉ አሉ

በቤልጄም ዋና ከተማ ብራሰልስ ዉስጥ ሶሻልና ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች በምህፃረ ቃሉ UNPO እየተባለ ከሚጠራ ውክልና ለሌላቸው ህዝቦች ተሟጋች ከሆነ አለማቀፍ ድርጅት ጋር በመተባበር ባዘጋጁት ኮንፍራንስ ላይ የተገኙት ታዋቂዉ ጋዜጠኛና የክሬት ትረስት ዳይሬክተር የሆኑት ግርሀም ፔብል ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ ምንግስት ሽብርተኛ መነስግሰት ነዉ በማለት እስከዛሬ ድረስ ብዙዎች እየተጠነቀቁ ሳያነሱት የሚያልፉትን የረጅም ግሴ እዉነት በአደባባይ ተናግረዋል። በዚህ አለም አቀፍ መድረክ ላይ በሴቶች ላይ እየተፈጸሙ ያሉ በደሎችን ጨምሮ አጠቃላይ በኢትዮጵያ ስላለውና እጅግ እየተባባሰ ስለመጣው የሰብአዊ መብት ጥሰቶችና ሰቆቃዎች ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

ኮንፍረንሱን እውቋ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋችና የአውሮፓ ፓርላሜንት አባል ማዳም አና ጎሜዝ፤ በእንግሊዝ የዲሞክራቲክ ፓርላሜንት ተወካይ ማዳም ጁሊ ዋር እንዲሁም የ UNPO ዋና ጸሃፊ ሚስተር ማሪኖ ቡስዳችን እንደመሩት ለማወቅ ተችሏል።

በኮንፍረንሱ በተናጋሪነት የተጋበዙት የቀድሞው የኦጋዲን ፕሬዜዳንት ልዩ አማካሪና የክልሉ ኮምኒኬሽን ተጠሪ የነበረውና በሱማሌ ክልል የተፈጸሙትን የሰብአዊ መብት ረገጣና ጥሰቶች የሚያጋልጡ ፊልሞችን ይዞ በመውጣት የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን ለአለማቀፍ ...... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የአርበኞች ግንቦት 7 እጩ ምልምል ወታደሮች ወጣቱን ኑና ተቀላቀሉን የሚል ጥሪ አቀረቡ

የአርበኞች ግንቦት 7 እጩ ምልምል ወታደሮች ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ለሚደረገው ትግል ዝግጁ መሆናቸውን የገለፁ ሲሆን ከፋሽስቱ ወያኔ ጋር ለሚደረገው የሞት ሽረት የነፃነት ትግል ወጣቱ ክፍል በነቂስ በመውጣት እንዲቀላቀላቸው ጥሪ አቅርበዋል። እጩ ምልምል ወታደሮች የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናቸው እንዲሰለፍም ጠይቀዋል። በኢትዮጵያ የተንሰራፋው በደል፤ ጭቆናና ዘረኝነት አንገሽግሾን ወደ ትጥቅ ትግል እንድንገባ አስገድዶናል የሚሉት እጩ ወታደሮቹ በምርጫ የሚመጣ አንዳች ለውጥ የለም በማለት ለውጥ ፈላጊው የኢትዮጵያ ወጣት ወደ ትጥቅ ትግሉ እንዲወጣና እንዲቀላቀላቀላቸው አበክረው ጠይቀዋል። አገራችንን ከጥፋት ህዝባችንን ከውርደትና ለመታደግ ሌላ የባዕድ ሃይል ሊመጣ ፈጽሞ አይችልም የሚሉት ወታደሮቹ አገራችንን ከዘረኛውና ከፋፋዩ የህወሃት አገዛዝ ነፃ ለማድረግ የመስዋዕትነት ተጋድሎ ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸው አሳስበዋል። በመጨረሻም በኢትዮጵያ ምድር ከፋፋይነት ተወግዶ አንድነት እንዲመጣና በዘረኛው የህወሃት አገዛዝ ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ከገባበት የጨለማ ህይወት እንዲወጣ ለማስቻል ህይወታቸውን ለመሰዋት ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

## 5 የአየር ሃይል የጥበቃ አባላትና 2 ፓይለቶች ጠፉ

ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የአየር ሃይል ምንጮች እንደገለጹት ከሁለት ሳምንት በፊት 5 የአየር ሃይል የጥበቃ አባላት እስከነ ሙሉ ትጥቃቸው እንዲሁም 2 ፓይለቶች ከድሬዳዋ አየር ሃይል ጠፍተዋል። የጥበቃ አባላቱም ሆነ ፓይለቶቹ ያሉበትን ለማወቅ የተደረገው ጥረት እስካሁን አልተሳካም። ይህንን ተከትሎ ጄ/ል ሳሞራ የኑስ ከሙቶ አለቃ ማእረግ በላይ ያላቸውን አየር ሃይል አባላት ሰብስበው ግምገማ አካሂደው ነበር።

ጄ/ል ሳሞራ "የአየር ሃይል አባላት ለምን ይከዳሉ? አሁን ያላችሁትስ ምን ታስባላችሁ?" የሚል ጥያቄ ለተሰብሳቢው ያቀረቡ ሲሆን፣ የአየር ሃይል አባላቱም ከፍተኛ የሆነ የአስተዳደር በደል እንደሚደርስባቸው፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ክፍያ እንደሚከፈላቸው፣ በመኖሪያ ቤት እጦት እንደሚሰቃዩ ገልጸዋል። መኮንኖቹ በርካታ ችግሮችን ዘርዝረው ያቀረቡ ቢሆንም፣ ጄ/ል ሳሞራ ችግሮችን ከመስማት ውጭ ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጡ ሄደዋል።

የአየር ሃይል አባላት ሞራል (ስሜት) መዳከም ገዢው ፓርቲ በሩሲያ ቅጥር አብራሪዎች ላይ እምነቱን እንዲጥል አድርጎታል። የትግራይ ተወላጅ የሆኑት ሻምበል ሳሙኤል ግደይ እና ቴክኒሻን ብርሃን ግደይ ከሙቶ አለቃ ቢልልኝ ደሳለኝ ጋር በመሆን ስርአቱን አናገለግልም ብለው ሄሊኮፕተር ይዘው መጥፋታቸው፣ የህወሃትን የዘር ፖለቲካ መሰረት እንዳናጋው ምንጮች ይገልጻሉ። ..... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የትግራይ ሕዝብንና የኢትዮጵያ ፓሊስን በኢትዮጵያዊያን ለማስጠላት የሚደረገው ጥረት ከሽፏል !

ህወሓት ንፁህንን ለመደብደብ የሚያበቃ በቂ ክፋት ያለው ልዩ ጦር ሲያሰለጥን ቆይቷል። ይህን ልዩ ጦር የፓሊስን መለያ እያለበሰ ነውረኛ ሥራዎችን እንዲሠራ በማድረግ በአንድ በኩል ንፁህንን የመጉዳት በሌላ በኩል ደግሞ ፓሊስን በሕዝብ የማስጠላት መንታ ግቦችን ለማሳካት ተጠቅሞበታል። ይህ ልዩ ጦር በአለፉት ጥቂት ሳምንታት ባዶ እጃቸው ለተቃውሞ በወጡ ነብሰ ጡር ሴቶች ላይ ሳይቀር ባሳየው ጭካኔ፣ በሰማያዊ እና በአንድነት ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ባደረሰው ድብደባ መጠን እና ባካሄደው የግለሰብ ንብረቶች ዝርፊያ የሥርዓቱ ባህርይ ፈጽሞ ከሰውኛ ተፈጥሮ እየወጣ እንደሆነ አመላካች ነው። በእነዚህ ድብደባዎች ወቅት በትግራይ ተወላጆች ላይ የተለየ ትኩረት በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስባቸው ተደርጓል። በትግራይ ተወላጆች ላይ የተለየ ትኩረት የተደረገው በደብዳቢዎቹ የግል ውሳኔ ሳይሆን ከበላዮቻቸው በተሰጠ ትዕዛዝ ነው ብሎ አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ያምናል።

በአርበኞች ግንቦት 7፡ እምነት መሠረት የፓሊስ ከፍተኛ አዛዦች ህወሓቶች ቢሆኑም አብዛኛው የሠራዊቱ አባል በህወሓት ዘረኛና ፋሽስታዊ አገዛዝ የተማረረ፣ የሥርዓቱ መለወጥ የሚፈልግና ሥርዓቱን ለመለወጥ የሚደረገውን ትግል የሚደግፍ ኃይል ነው። ስለሆነም ህወሓት የተለየ ጦር አሰልጥኖ የፓሊስ ልብስ በማልበስ ነውረኛ ወንጀል በማሠራት ፓሊስን ለማስጠላት የሚያደርገው ሴራ ሊጋለጥ ይገባል ብሎ ያምናል። የፓሊስ ሠራዊት አባላትም በስማቸውና በደንብ ልብሳቸው የሚደረገውን ደባ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንዲያጋልጡ አርበኞች ግንቦት 7 ያሳስባል።

ህወሓት እንደሚያስበው እና የኢትዮጵያም ሕዝብ እውነት አድርጎ እንዲቀበለው እንደሚፈልገው የትግራይ ሕዝብ በጅምላ የህወሓት አፍቃሪና ደጋፊ አይደለም። እንዲያውም በተፃፃሪው ህወሓት ከትግራይ ተወላጆች ልብ እየተነቀነ ነው። የትግራይ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትሕዴን/ደምህት) ከትግራይ የበቀለ፣ ህወሓትን በአመጽ ለመፋለም የቆረጠ ኃይል ነው። አርበኞች ግንቦት 7 በትግራይ ውስጥ ብዙ ደጋፊዎች ያሉት መሆኑ የምናውቀው ሀቅ ነው። አረና ትግራይ ህወሓትን በሰላማዊ መንገድ ለመታገል የተነሳ ተሰሚነቱን በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣ እና አቶ አብርሀ ደስታን የመሰለ ወጣት ኢትዮጵያዊ የፓለቲካ መሪ ያወጣ ድርጅት ነው። ህወሓት አንድነት ፓርቲ ላይ የመረረ አቋም ከወሰደባቸው ምክንያቶች አንዱ በትግራይ ውስጥ ያለው ተቀባይነት በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ መምጣቱ ነው። ህወሓት የትግራይን ሕዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በጅምላ ለማጣላት የሚያደርገው ጥረት ማክሸፍ ይኖርብናል ብሎ አርበኞች ግንቦት 7 ያምናል፤ ለዚህም ተግቶ ይሠራል። አርበኞች ግንቦት 7 ከትግራይ የዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር በመተባበር ፀረ ህወሓት ትግል በትግራይ ውስጥ መቀጣጠል ይኖርበታል ብሎ ያምናል። በዚህም መሠረት ትግራይ የህወሓት መቀበሪያ የመሆኗ ጊዜ ሩቅ አይደለም።

በዘንድሮው የ2007 የሴራ ምርጫ አማካይነት ተድበስብሰው የመጡ እነዚህ ሁለት ክፋቶች ማለትም ፓሊስን በሕዝብ ማስጠላት እና የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የዲሞክራሲ ወገንተኞችን ለይቶ ማጥቃት ከበስተጀርባቸው ያዘሉት እኩይ ዓላማ መጋለጡ መንገዳችን ያጠራልናል ብሎ አርበኞች ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል። በአንድነትና በመኢአድ የተፈፀው የድርጅትና የንብረት ዘረፋም የዚሁ ፕሮጀክት አካል መሆኙ ግልጽ ነው፤ ነገ ተመሳሳይ ነገር በሰማያዊ ፓርቲም ላይ ይፈጽም ይሆናል።

በመሆኑ ከ2007 የሴራ ምርጫ ትሩፋቶች በትግራይ ሕዝብና በፓሊስ ሠራዊት ጀርባ የሚደረገው ደባ መጋለጡ ነው። ይህ ድል ጽኑ መሠረት እንዲይዝ ህወሓትንና የትግራይን ሕዝብ የመነጠል እና ፓሊስ የሕዝብ አጋር መሆኑን የማረጋገጥ ሥራዎችን አጠናክረን መሥራት እንዳለብን አርበኞች ግንቦት 7 ያሳስባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## ታዋቂዉ ጋዜጠኛ ግርሀም ፔብል ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ማህበረሰብ በማጋለጥ ላይ የሚገኘው ወጣት አብዱላሂ ሁሴን፤ ተቀማጭነታቸው በጀኔቭ ስዊዘርላንድ የሆኑት የአፍሪካ የሰብአዊ መብት ተሟጋች አቶ አብዱላሂ ሙሃመድ፤ ወጣት የኦጋዴን ሴቶች ተወካይ ወ/ሪት ጃዌሪያ ቢሲይ፤ ሚስተር ግርሃም ፒብልስ ጋዜጠኛና የክሬት ትረስት ዳይሬክተር፤ እንዲሁም ዶ/ር ባሮ ቀኖ በኦሮሞ ሴቶች ላይ ስለተፈጸሙ ወሲባዊ ትንኮሳዎችና አሰቃቂ የመደፈር ወንጀሎች በተመለከተ ያጠኑትን ጥናት በመድረኩ ላይ ያቀረቡ ሲሆን ከፓለቲካ ድርጅቶች የኦጋዴን ነፃነት ግንባር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት ዶ/ር ባደል አህመድ ሃሰንና የአርበኞች ግንቦት 7 ንቅናቄ ከፍተኛ አመራር አቶ አበበ ቦጋለ መሆናቸውን ለማወቅ ችለናል።

የኮንፍረንሱ ተናጋሪዎች የተመቻቸላቸውን መድረክ በመጠቀም በተለይ የፋሺስቱ ወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያን ላይ እየፈጸማቸው ስላሉት መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ጨምሮ የፓለቲካ እንዲሁም የመናገር ነፃነት ጥሰቶችን በስፋት በመተንተን ለኮንፍረንሱ ተሳታፊዎች አስረድተዋል።

የንቅናቄያችን ከፍተኛ አመራር የሆኑትና በኮንፍረንሱ የተካፈሉት አቶ አበበ ቦጋለ ባደረጉት ንግግር ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሚመራት ኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ያለው መጠነ ሰፊ አፈናና ሰቆቃ በዋናነት ፋይናንስ የሚያደርገው በአለማቀፉ ህብረተሰብ በተለይም የአውሮፓ ህብረትና አሜሪካ በብድርና በእርዳታ በሚሰጡት ገንዘብ መሆኑን በማጋለጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማና መረጋጋት እንዲሰፍን የሚሻ ማንኛውም አገር ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነታቸው እያደረጉት የሚገኙትን ትግል በሃይል እየጨፈለቀ ላለው አምባገነኑ የሕወሓት አገዛዝ የሚያደርጉትን እርዳታም ሆነ ብድር ማቆም አለባቸው ብለዋል። ይህ ማድረግ ካልቻሉና ድጋፍም ሆነ እርዳታ ለፋሺስታዊው አገዛዝ መስጠት የሚቀጥሉ ከሆነ ለወዳጅነታቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ይልቅ ነገ የታሪክ ትቢያ ለሚሆነው የወያኔ አገዛዝ ያደሉ መሆናቸውን እንዲረዱ አበክረው አስገንዝበዋል። በተጨማሪም ወያኔ በይ 5 አመቱ ለሚያደርግው የይስሙላ ምርጫ የአውሮፓ ህብረትና አባል መንግስታት በብዙ ሚሊዮን ዮሮ የሚገመት ገንዘብ እያፈሰሱ ፍጹም የሌለ እና ኢፍትሃዊ የሆነ ምርጫ በመታዘብ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አምባገነኖችን ከማንገስ እንዲታቀቡ ጥሪ አቅርብዋል።

የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር ተወካይ በበኩላቸው ፋሽስቱ ወያኔ በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው አረመኔያዊ ሰቆቃ ቀድም ሲል የነበሩ መንግስታት ከፈጸሙት በመጠንም በጭካኔም እጅግ የከፋ መሆኑን አስረግጠው በመናገር አለማቀፉ ህብረተሰብ ችግሩን እያየና እየታዘበ እንዳላየ በመምሰል ህዝቡ ከሚደርስበት ሰቆቃ ብዛት ወደ ጽንፈኝነትና አካራሪነት ጎራ በመቀላቀል አካባቢውን ለትርምስ እንዳይዳርጉ እርምጃ ለመውሰድ ጊዜው አሁን ነው ሲሉ አሳስበዋል። የኢትዮጵያ ህዝብም በኦጋዴን ወንድሞቹ ላይ የሚደርሰውን በደል እንደራሱ በደል በመቁጠር የበደልና የሰቆቃ መሰረት የሆነውን ፋሽስታዊ አገዛዝ እድሜ ለማሳጠር የሚደረገውን ትግል እንዲቀላቀሉ ጥሪ አቅርበዋል።

የዕለቱ ኮንፍረንስ መሪ የነበሩት ማዳም አና ጎሜዝና ሚስተር ማሪዮ ቡስዳሽን የአውሮፓ ህብረት በዘንድሮው ምርጫ ምንም አይነት ታዛቢ እንደማይልክ መወሰኑን በመግለጽ ኢትዮጵያኖች በፋሽስታዊው የወያኔ አገዛዝ ከሚደርስባቸው እጅግ አረመኔያዊ ሰቆቃና አፈና የሚታደጋቸው ሃይል ከውጭ ከመጠበቅ ይልቅ ዘረኛው ወያኔ ከፋፍሎ ለመግዛትና የአገዛዝ እድሜውን ለማርዘም በመካከላቸው የገነባውን የዘርና የጥላቻ ግንብ በመናድ በጋራ ተቀራርበውና ተደጋግፈው እንዲነሱ አበክረው በማሳሰብ ላለፉት 24 አመታት ከላያቸው ተጭኖ እየገደላቸው፤ እያሰራቸውና እያሰደዳቸው ያለውን ፋሺስታዊ አገዛዝ ለማስወገድ በጽናት መታገል ይኖርባቸዋል ሲሉ ለኢትዮጵያውያን ጥሪ አስተላልፈዋል።

እ.ኤ.አ በ 2013 እና በ2014 በኢትዮጵያ ውስጥ እንደነበሩ የገለጹትና በሁለት አመታት ቆይታቸው የተመለከተቱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እጅግ ስሜት የሚነካና የሚያሳዝን ነው ያሉት ጋዜጠኛና የክርኤት ትረስት ዳይሬክተር ሚስተር ግርሃም በተለይ በኦጋዴን ክልል ያነጋገሯቸውን ሰቆቃ የተፈጸመባቸውን ሰዎች ሁኔታ ሲያስርዱ በውይይቱ ላይ የተሳተፉ የአውሮፓ ህብረት ባለስልጣናትና ተጋባዥ እንግዶች በከፍተኛ ሃዘን ውስጥ ወድቀው መታየታቸውን ተባባሪ ዘጋቢያችን አመልክቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኮንፍረንሱ ላይ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን አቋም እንዲገልጽ በብራስልስ የሚገኘው የወያኔ ኢንባሲ የተጋበዘ ቢሆንም ኢንባሲው ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ግለሰብ መላኩንና በዜግነት ቤልጄማዊ የሆነ ሚስተር ጆሃን የተባለ የኢንባሲቅ ቅጥረኛ መገኙትን ለማወቅ ተችሏል። የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ለሆዳቸው ያደሩ ጥቂት ኢትዮጵያኖችን በመጠቀም እየሰራ ባለው ስራ ላይ እምነት እያጣ በመምጣቱ የውጭ ዜጎችን በመቅጠር በመሰል ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ በማድረግ የተነሱትን ሃሳቦች እንዲሁም በየ ስብሰባዎቹ የተገኙ ሰዎችን መረጃ በመሰብሰብ ስራ ላይ መጠመዱን የገለጹት በኮንፍረንሱ የተገኙት የንቅናቄያችን ከፍተኛ አመራር አቶ አበበ ቦጋለ ይህም ፋሺስታዊው አገዛዝ ታማኞቼ ናቸው ይላቸው በነበሩ ጥቂት ግለሰቦች ሳይቀር እየተተፋ መምጣቱንና አገዛዙ እርቃኑን እየቀረ መሄዱን ያሳያል ሲሉ ለሬዲዮ ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል።

## ለወያኔ ዉንብድና መልሱ ህዝባዊ እምቢተኝነትና ህዝባዊ አመጽ ነዉ!

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎ የኢትዮጵያን በትረ ስልጣን ጨብጠዉ በኖሩባቸዉ ባለፉት ሃያ አራት አመታት የአገራችን የኢትዮጵያን የፖለቲካ መድረክ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እጅግ በጣም ከዘቀጠና ከረከሰ የወያኔ ድራማ ዉጭ ሌላ ምንም ነገር የማይታይበት አለባሌ መድረክ አድረገዉት ቆይተዋል አሁንም እያደረጉት ነዉ። አንድ ቋንቋ የሚናገሩትና ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸዉ የወያኔ መሪዎች ኢህአዴግ የሚባል አጋሰስ የሽፋን ድርጅት ፈጥረዉ በኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊ መብትና ነጻነትና ላይ ተነግሮም ተጽፎም የማያልቅ ግዙፍ ግፍና በደል ፈጽመዋል። ህጻን፤አዛዉንት፤ ወንድና ሴት ሳይለዩ መብቴን አትንኩ ያለቸዉን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያለምንም ርህራሄ በጥይት ጨፍጭፈዋል። ሴቶች እህቶቻችንን እጅና እግራቸዉን አስረዉ ጡታቸዉን በመቆንጠጫ እየቆነጠጡ በሴትነታቸዉ ላይ የዉርደት ተግባር ፈጽመዋል። ወንዶች ወንድሞቻችንን ደግሞ ዉስጥ እግራቸዉን ገልብጠዉ እየገረፉ ጥፍራቸዉን አይናቸዉ እያየ በጉጠት እየሳቡ ነቅለዋል። ባጠቃላይ የወያኔ ዘረኞች በዛሬዉ ዘመን አንኳን ወገን በወገኑ ላይ የዉጭ ጠላትም በህዝብ ላይ የማይፈጽመዉ በደል በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ፍጽመዋል።

ወያኔ ስልጣን እንደያዘ "አባይ ትግራይ" ወይም "ታላቋ ትግራይ" የሚለዉን ህልሙን ለማሳካት ወልቃይት ጠገዴን ከጎንደር ቆርሶ ከትግራይ ጋር ቀላቅሏል። ስልጣን ይዞ ከተደላደለ ከአመታት በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያን ገበሬ ከመሬቱ አፈናቅሎ ለምለም መሬቱን በርካሽ ዋጋ ለባዕዳን ሸጧል፤ ከዚህ አልፎ ተርፎም የአባቶቻችን አጽም ያረፈበትን የአገራችን ዳር ድንበር ቆርሶ ለጎረቤት አገር ገጸ በረከት አቅርቧል። ይህ አገራቸዉንና የሚመሩትን ህዝብ በሚጠሉ ጠባቦች የተሞላ ድርጅት ባለፈዉ ሳምንት የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ደጋፊዎቹንና በአንቀልባ ታዝለዉ አስከዛሬ ያቆዩትን ምዕራባዉያን ጭምር ግራ ያጋባ ፀረ አገርና ፀረ ህዝብ እርምጃ ወስዷል። ድርጅት እያፈረሰና በፓርቲ ላይ የራሱን ተለጣፊ ፓርቲ እያቋቋመ ዛሬ ላይ የደረሰዉ ወያኔ ምርጫ የሚባል ድራማ በደረሰ ቁጥር የሚይዘዉ በሽታ ዘንድሮም ይዞት አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲንና መላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅትን አፍርሶ በምትካቸዉ የራሱን መኢአድና የራሱን አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ፈጥሯል። ይህ ወያኔ ከሰሞኑ የወሰደዉ የፖለቲካ እርምጃ በየትኛዉም አለም በተለይ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዐትን እንከተላለን በሚሉ አገሮች ዉስጥ ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ እጅግ በጣም ትልቅ የፖለቲካ ሸፍጥ ነዉ።

የወያኔን ታሪክ ተወልዶ ካደገበት ከደደቢት በረሃ እስከ ሚኒልክ ቤ/መንግስት ድረስ ያደረገዉን ጉዞ ስንመለከት ወለል ብሎ የሚታየን አንድ ሐቅ አለ፤ እሱም ወያኔ ሁሉንም ነገር በዘር መነጽር ብቻ የሚመለከትና ህዝብን በወዳጅና በጠላት ጎራ ለይቶ ወዳጅ አይደለም ያለዉን ሁሉ እንደ ሩሲያዊዉ ዮሴፍ ስታሊን እየገደለ የመጣ ድርጅት ነዉ። በእርግጥም ወያኔ ጫካ ዉስጥ እያለም ሆነ ዛሬ ከተማ ገብቶ የሚቃወመዉንና በሀሳብ የማይግባባዉን ድርጅትም ሆነ ግለሰብ እያፈረሰና እገደለ ባፈረሳቸዉ ድርጅቶች ምትክ ደግሞ የራሱን ተለጣፊ ድርጅት እየፈጠረ የመጣና ከዲሞክራሲያዊ አሠራርና ከስልጣኔ ጋር የማይተዋቀ ድርጅት ነዉ።

በመርፌ የተጠቃቀመ ቁምጣና ጥብቆ ለብሶ አስራ ሰባት አመት ጫካ ለጫካ የተጓዘዉ ወያኔ ጎንደር፤ ጎጃምና አምቦ እያለ ወደ አዲስ አበባ ሲጠጋ ከተገነዘባቸዉ ነገሮች አንዱ የለበሰዉ የተጠቃቀመ ቁምጣ የትም እንደማያደርሰዉና ለከተማ ኑሮ የሚስማማ አዲስ ልብስ እንደሚያስፈልገዉ ማወቁ ነዉ። በጥላቻ ተረግዞ በክፋት ላደገዉ ወያኔ ቢበቃዉም ባይበቃዉም ወይም ቢያምርበትም ባያምርበትም ይህንን ለከተማ ዉስጥ ኑሮ የሚያስፈልገዉን አዲስ ልብስ ለማዘጋጀት ብዙ ግዜ አልወሰደበትም። የሚሰርቅና የሚስቅ ምን ግዜም ተባባሪ አያጣም እንዲሉ ወያኔ የአዲስ አበባን መሬት የረገጠዉ ጦር ሜዳ ላይ የማረካቸዉን ወታደሮችና አገር ዉስጥ ያገኛቸዉን ደካማ ሰዎች ሰብስቦ በፈጠረዉ ኢህአዴግ በሚባል ፈረስ ጀርባ ላይ ተፈናጥጦ ነበር። ትግራይን ነጻ አወጣለሁ ብሎ ትግል የጀመረዉ ወያኔ ኢህአዴግን የፈጠረዉ ወያኔነቱን ለመተዉ ሳይሆን እራሱን በዚህ በኢትዮጵያ ስም በፈጠረዉ ድርጅት ዉስጥ ሸሽጎ እዉነተኛ ባህሪዩን ለመደበቅ ነበር።

ከግንቦት 1983 ዓም አስከ ግንቦት 1987 ዓም ድረስ የዘለቀዉንና በወያኔ የበላይነት ተጀምሮ ወያኔን በማንገስ የተጠናቀቀዉን የሽግግር መንግስት ወደ ኋላ መለስ ብሎ የቃኘ ማንም ሰዉ የወያኔን ሁለት ዋና ዋና መሠሪ ስራዎች በቀላሉ መመልከት ይችላል።

**አንደኛ-** አነግንና የደቡብ ህዝብ ንቅናቄን ጨምሮ አያሌ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና ታዋቂ ግለሰቦችን አቅፎ ስራዉን የጀመረዉ የሽግግሩ መንግስት የስራ ዘመን የተገባደደዉ የኢትዮጵያን አንድነት ጥያቄ ያነሱ ግለሰቦችን በማሰርና ከወያኔ ቁጥጥር ዉጭ እራሳቸዉን ችለዉ ለመንቀሳቀስ የሞከሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ከሽግግሩ መንግስት በማባረር ነበር።

**ሁለተኛ-** ወያኔ የኋላ ኋላ እያደር ለመስራት ላቀዳቸዉ አገር የመበተንና ህዝብን የመለያየት ስራዎች እንዲያመቸዉ ከእያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት ጀርባ የኢትዮጵያ ህዝብ ተለጣፊ እያለ የሚጠራቸዉን ድርጅቶች በራሱ አምሳል እየፈጠረ ማሰማራቱ ነዉ።

ባጠቃላይ ወያኔ የፈጠረዉ የሽግግር መንግስት ኢትዮጵያዊ አጀንዳና አገራዊ ራዕይ ይዘዉ የተንቀሳቀሱ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን አጥፍቶ ወያኔን ዘለአለማዊ ንጉስ ለማድረግ ከመሞከሩ ዉጭ ሌላ ምንም ኢትዮጵያን የሚጠቅም ስራ አልሰራም።

ከሽግግሩ መንግስት በኋላ ወያኔ ተወዳዳሪዉም አሸናፊዉም እሱ ብቻ የሆነባቸዉን ሁለት ትርጉም የለሽ ምርጫዎችን አካሂዷል።እነዚህን ተወዳዳሪ የለለባቸዉን ሁለት ምርጫዎች በቀላሉ በማሸነፉ ህዝብ የወደደዉ መስሎት ልቡ ያበጠዉ ወያኔ ሦስተኛዉን አገራዊ ምርጫ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ምርጫዎች በተለየ መልኩ ለቀቅ አድርጎ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ፤ መራጩን ህዝብ መቅረብ እንዲችሉና ወያኔን እራሱን ምርጫዉን አስመልክቶ ክርክር እንዲገጥሙት በሩን ከፈተላቸዉ። ነገሩ "የማይነጋ መስሏት" እንዲሉ ሆነና ሜዳዉም ፈረሱም ይሄዉና ብሎ የፈልሚያዉን ሜዳ የከፈተዉ ወያኔ የምርጫዉ ቀን ደርሶ በዝረራ መሸነፉን ሲሰማ በራሱ ሜዳና በራሱ ዳኞች ፍት ያሸነፉትን የህዝብ ተመራጮች ከየመኖሪያ ቤታቸዉ እያደነ አስሮ በአገር ክህደት ወንጀል ከሰሳቸዉ ። የሚገርመዉ ወያኔ በምርጫዉ ተወዳድረዉ በምስክር ፊት በአደባባይ ያሸነፉትን የህዝብ ተመራጮች በማሰር ብቻ አልተወሰነም። በወቅቱ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አይኑ ብሌን ይመለከተዉ የነበረዉን ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲን አፍርሶ እንደለመደዉ የራሱን ቅንጅት ፓርቲ ፈጥሮ ይበኽል ብሎ ላሰባቸዉ ደካማና ሆዳም ግለሰቦች አስረክቧል።

ይህ ቆየት ያለ በሽታዉ ዘንድሮም አገርሽቶበት አንድነትንና መኢአድን ለከፏቸዋል። ይህ ወያኔ ከሰሞኑ መኢአድና አንድነት ላይ የወሰደዉ እርምጃ እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች በመጪዉ ምርጫ ላይ ያሸንፉኛል ከሚል ፍራቻ አይደለም። ወያኔ ምርጫዉ የሚካሄድበት ሂደት ብቻ ሳይሆን ህዝብ የሰጠዉ ድምጽ የሚቆጠርበትና የምርጫዉ ዉጤት ለህዝብ የሚገለጽበት መንገድ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ስር እንደሆነና ይህንን ምርጫ ብቻ ሳይሆን የሚቀጥለዉንም ምርጫ ከሱ ዉጭ ሌላ ማንም እንደማያሸንፍ በሚገባ ያዉቃል። ወያኔ መኢአድንና አንድነትን የጥቃቱ ሰለባ ያደረጋቸዉ ህዝባዊ አላማቸዉንና አገራዊ ራዕያቸዉን በተለይ እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ፤ አንድነትና እኩልነት ጥያቄ ላይ ያላቸዉን የጠራና የማያወላዉል አቋም እጅግ በጣም ስሚጠላ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ እንዲህ በአጭር ግዜ ዉስጥ መኢአድንና አንድነትን የጨፈለቃቸዉ እነዚህ ሁለት አንጋፋ ፓርቲዎች አዲስ አበባን ጨምሮ በየክልሉ የዘረጉት መዋቅርና ከህዝብ ጋር የፈጠሩት የቅርብ ግኑኝነት እንቅልፍ ስለነሳዉ ነዉ። ሌላዉ በፍጹም መርሳት የሌለብን ነገር ቢኖር ይዋል ይደር እንጂ ወያኔ እኛ ቀድመን ካላጠፋነዉ በቀር "ኢትዮጵያዊነት" ፤ "አንድነት" ወይም ፍትህና ነጻነት ብሎ የተነሳን ማንንም ኢትዮጵያዊ ግለሰብ ወይም ድርጅት ማጥፋቱ አይቀርም። በእርግጥም ከትናንት ወዲያ ቅንጅትን፤ ዛሬ ደግሞ መኢአድንና አንድነትን አፍርሶ የራሱን ተለጣፊ አሻንጉሊቶች የፈጠረዉ ወያኔ ነገ እነዚህ ፓርቲዎች የቆሙለትን አላማ የተሸከምነዉን ኢትዮጵያዉያን አንድና ሁለት እያለ ለቃቅሞ እንደሚያጠፋን ምንም ጥርጥር የለዉም።

ወያኔ አምስት አመት አየቆየ በሚመጣዉ የምርጫ ድርማ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ ላይ እንደማይወርድ በ1997 ዓም ሰኔ ወርና በ 1998 ዓም ህዳር ወር በአዲስ አበባ አደባባዮች ላይ በወሰደዉ ፋሺስታዊ እርምጃ በግልጽ አሳይቶናል።ከላይ ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረዉ ወያኔ ፊታችን ላይ ባለዉ በ2007ቱ ምርጫ ወይም በተከታታይ በሚመጡት ምርጫዎች ተሸንፎ ከስልጣን እወርዳለሁ የሚል ምንም አይት ስጋት የለበትም፤ ምክንያቱም በምርጫዉ ጨዋታ ዉስጥ ተጫዋቹም ፤ ሜዳዉም ዳኛዉም ወያኔ ብቻ ነዉ። ዛሬ የወያኔን መሪዎች ያንቀጠቀጣቸዉና እንዳበደ ዉሻ ያገኙትን ሁሉ እንዲነክሱ ያደረጋቸዉ አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ በተግባራዊ ስራዎች ላይ መናበብ በመጀመሩና በህዝባዊ እምቢተኝነቱና በህዝባዊ አመጹ ዘርፍ የሚደረገዉ እንቅስቃሴ ህዝባዊ ሙቀት አግኝቶ እየተጋጋለ በመምጣቱ ነዉ። ወያኔዎች እነሱንና የገነቡትን ዘረኛ ስርዐት ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርጎ የሚያጠፋዉ የህዝባዊ አመጹና የህዝባዊ እምቢተኝነቱ ጎርፍ መሆኑን ካወቁ ቆይተዋል። ይህ ከሰሞኑ በማሰር፤ በመደብደብና ድርጅት በማፍረስ የወሰዷቸዉ እርምጃዎች የሚያሳዩን ወያኔዎች ህዝባዊ ጎርፉን ቢቻል ለማጥፋት አለዚያም ጉዳት በማያደርስ መልኩ ለመገደብ ያሚያደርጉትን ከንቱ ሙከራ ነዉ።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፤ የኢትዮጵያ ወጣት፤ ገበሬና ሰራተኛ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ትናንት ቅንጅትን አፍርሶ የራሱን መናኛ ቅንጅት የፈጠረዉ ወያኔ ዛሬም እንደገና አሉ የሚባሉትንና አገራዊ ራዕይ ይዘዉ የሚንቀሳቀሱትን አንድነትንና መኢአድን አፍርሶ ..... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ኦሮምያ ዉስጥ ቅስቀሳ ለማድረግ የሄዱ የኦፌኮ አባላት ምግብና አልጋ እንዳይዙ አስደረገ

የኦሮሞ ፌደራሊስ ኮንግረስ ምክትል ሰብሳቢ አቶ ሙላቱ ገመቹ፣ የክልል ምክር ቤት አባላትንና የተወካዮች ምክር ቤት አባላትን ለማስመዝገብ በተንቀሳቀሱበት ወቅት አልጋና ምግብ እንዳያገኙ ተከልክለው እንደነበር ገልጸዋል። ከደምብቢ ዶሎ ወደ ጊምቢ ሲሄዱ አይራ በሚባል ቦታ ላይ ለማደር አንድ ሆቴል ውስጥ አልጋ ለመያዝ ሲሞክሩ፣ ፖሊሶች ለሆቴሉ ባለቤት በመደወል አልጋ እንዳይሰጡዋቸው፣ ምግብም እንዳይሸጡላቸው ማዘዛቸውን ተናግረዋል። የሆቴሉ ባለቤት ከደህንነት መስሪያ ቤት ተደውሎ "ወንጀለኞች ናቸውና አባሩዋቸው" ተብሎ እንደተነገራቸው አቶ ሙላቱ አክለው ተናግረዋል።

ባለሆቴሉ "ንግድ ቤቴን ይዘጉብኛል ብለው በመማጸናቸው" 4ቱም ሰዎች መኪና ውስጥ ለማደር መገደዳቸውን ገልጸዋል። በማግስቱ ጉሊሶ ወደምትባል ከተማ ሄደው ሆቴል ከያዙ በሁዋላ ምሽት ላይ የታጠቁ ፖሊሶች ወደ ክፍላቸው ገብተው ፍተሻ እናካሂዳለን በማለት ውዝግብ ፈጥረው እንደነበር አውስተዋል። ምርጫው ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ይሆናል የሚባለው ተረት ነው ያሉት አቶ ሙላቱ፣ ጉዳዩን ለምርጫ ቦርድ ማሳወቃቸውን ቢገልጹም፣ ኢህአዴግ ይህ የድርጅት ጉዳይ ሳይሆን ግለሰቦች ያደረጉት ነው በማለት ለማጣጣል መሞከሩን ተናግረዋል በሌላ በኩል ደግሞ በደቡብ ክልል የአንድነት የአመራር አባላት ታሰረዋል።

የምርጫ ቦርድ በአንድነት ፓርቲ ላይ የወሰደውን እርምጃ የተቃወሙ የቁጫ የአንድነት ሰብሳቢ አቶ ኢሳያስ ቱሉ ና አቶ ጌታቸው ኩየራ ተይዘው ሲታሰሩ፣ የስልጤ ዞን ሰብሳቢ አቶ ኢብራሂም ከድር  ደግሞ ከስራ ተባረዋል። በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ የአንድነት ፓርቲ አባላት የምርጫ ቦርድን ውሳኔ በመቃወም ፔትሺን ተፈራርመው ለምርጫ ቦርድ አስገብተዋል። ሰማያዊ ፓርቲ እንደገለጸው ደግሞ፤ ምርጫ ቦርድ በአንድነት ፓርቲ ላይ ውሳኔ ማስተላለፉን ተከትሎ የቀድሞ የአንድነት አባላት በስፋት ሰማያዊ ፓርቲን እየተቀላቀሉ ይገኛሉ።

ትናንት ጥር 28/2007 ዓ.ም በአምስት የምርጫ ወረዳ የተደራጁት የቀድሞው አንድነት ፓርቲ የቦረና ዞን መዋቅር ሙሉ በሙሉ ሰማያዊ ፓርቲን መቀላቀላቸውን የአንድነት መስራች፣ የምክር ቤት አባልና የዞኑ የፓርቲው አደራጅ የነበሩት አቶ ጌታቸው በቀለ ገልጸዋል። ከዚህም ባሻገር የቡርጅና የሰሜን ቀጠና አስተባባሪዎችን ጨምሮ  የቀጣናው መዋቅር በሙሉ ሰማያዊ ፓርቲን መቀላቀሉ ተመልክቷል። እንደ ፓርቲው ገለጻ፤ ጥር 26/2007 ዓ.ም የቀድሞው የአንድነት አመራሮች ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር መቀላቀላቸውን በመግለጫ ካሳወቁ በኋላ በአዲስ አበባና በሌሎች አካባቢዎች የሚኖሩ የቀድሞው የአንድነት አመራሮችና አባላት ያለማቋረጥ ሰማያዊ ጽ/ቤት ድረስ እየመጡ የአባልነት ቅጽ እየሞሉ ይገኛሉ።

ሰማያዊን የተቀላቀሉት የአንድነትአመራሮችና አባላት፤ ገዥው ፓርቲና ምርጫ ቦርድ ፓርቲያቸውን አሳልፈው መስጠታቸው የተፈጠረባቸው ቁጭት፤ ይበልጥ ሰላማዊ ትግሉን አጠናክረው እንዲቀጥሉ እንደገፋፋቸው ተናግረዋል። ሙሉ መዋቅራቸውን ይዘው ወደ ሰማያዊ ፓርቲ የተቀላቀሉት የቦረናው አደራጅ አቶ ጌታቸው በቀለ፤ ገዥው ፓርቲና ምርጫ ቦርድ በፈጸሙት በደል ተስፋ ሳይቆርጡ እንደሚታገሉ በመጥቀስ ህዝቡም ተስፋ ሳይቆርጥ የቻለውን ሁሉ በማድረግ ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ አቅርበዋል።

## በአማራና ትግራይ ድንበር የተነሳውን ውዝግብ ለመፍታት የተጠራው ስብሰባ ተበተነ

በአማራና በትግራይ ክልል ድንበሮች አካባቢ የተነሳውን ችግር ለመፍታት ከፌደራል መንግስት፣ ከትግራይና ከአማራ ክልል የተውጣጡ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ጥር 26 ቀን 2007 ዓም ከሁለቱም ክልሎች የተውጣጡ 300 ነዋሪዎችን ሰብስበው ያነጋገሩ ቢሆንም፣ መግባባት ሳይቻል በመቅረቱ ለየካቲት 4 በድጋሜ መቀጠሩን የአካባቢው ምንጮች ገልጸዋል። የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማርያም፣ የአማራ ክልል ፐ/ት ገዱ አንዳርጋቸው፣ የትግራይ ክልል ፐ/ት አባይ ወልዱ፣ ቴዎድሮስ ሃጎስ፣ የሰሜን ምእራብ እዝ አዛዥ ሌ/ጄ ብርሃኑ ጁላ፣ የመከላከያ ዘመቻ ሃላፊ ሜ/ጄኔራል ገብረእግዚአብሄር መብራቱ እና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣኖች በስብሰባው ላይ ተገኝተዋል።

በመጀመሪያው ቀን ስምምነት ባለመደረሱ በማግስቱ ከሁለቱም ክልሎች የተውጣጡ 30  ነዋሪዎች ከባለስልጣናቱ ጋር ተሰብስበው የነበረ ቢሆንም፣ አሁንም ሳይሳሙ በመቅረታቸው ለየካቲት አራት ቀጠሮ ይዘው ተለያይተዋል። በአማራ ክልል በኩል የሚኖሩ ነዋሪዎች የትግራይና የአማራ ክልሎች ድንበር ተከዜ ሆኖ እያለ፣ ክልሉ ከዚህ ቀደም በጉልበት ከተከዜ በመሻገር  ሁመራ እና  ዳንሻ የመሳሰሉ ቦታዎችን መቆጣጠሩንና አሁን ደግሞ እስከመተማ ያለውን ቦታ በመያዝ ሰሜን ጎንደርን በግማሽ ለማጠቃለል ያስባል በማለት የክልሉን የመስፋፋት ፖሊሲ ተቃውመዋል።

በትግራይ ባለስልጣናት በኩል ደግሞ  የክልሉ ድንበር እስከመተማ ይደርሳል የሚል አቋም የተንጸባረቀ ሲሆን፣ የአካባቢው ነዋሪዎች የያዙት አቋም የትግራይ ክልል ባለስልጣናትን አበሳጭቷል። በአካባቢው ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰራዊት አባላትና የፌደራል ፖሊሶች የተሰማሩ ሲሆን፣ ህዝቡን ያስተባብራሉ የተባሉ የአካባቢው መሪዎች እየተለቀሙ በመታሰር ላይ ናቸው። በአካባቢው ያለው ውጥረት በቀላሉ አይበርድም የሚሉት ነዋሪዎች፣ ችግሩ ቶሎ ካልተፈታ ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል በማለት ያስጠነቅቃሉ።

በቋንቋና ዘር ላይ የተመሰረተ የፌደራል ስርዓት ከተመሰረተ ጊዜ አንስቶ በክልሎች መካከል የሚታየው የድንበር ውዝግብ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው። በኦሮምያና በሶማሊ፣ በኦሮምያና በደቡብ፣ በአፋርና በአማራ፣ በአማራና በትግራይ፣ በደቡብና በጋንቤላ፣ በትግራይና አፋር እንዲሁም በሶማሊና በአፋር ባልተፈቱ የድንበር ግጭቶች በርካታ ዜጎች አልቀዋል።

## መቶ አለቃ ተሰማ ወንድሙ ወያኔ  ባደረሰባቸው ድብደባና መድህኒት ክልከላ ህይወታቸው አለፈ

የ9ኙ ፓርቲዎች በጠራው የአዳር ሰልፍ ታስረው የነበሩት  የመቶ አለቃ ተሰማ ወንድሙ በእስር ቤት ሳሉ በደረሰባቸው ድብደባና መድህኒት ክልከላ ህይወታቸው ማለፉን ነገረ-ኢትዮጰያ ዘገበየመላው አማራ አንድነት ድርጅት ምክትል ጸሀፊ የሆኑት መቶ አለቃ ተሰማ ወንድሙ የህዳር 27/28 የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር በጠራው የአዳር ሰልፍ ላይ  ነው ክፉኛ  የተደበደቡት። የስኳር ህመምተኛ የሆኑት የመአህድ ምክትል ጸሀፊ ከደረሰባቸው የከፋ ድብደባ ባሻገርም   ወደ እስር ቤት ተወስደው  ለሶስት ተከታታይ ቀናት  መድሃኒት እንዳይገባላቸው መከልከላቸው  ለከፋ ህመም እንደዳረጋቸው ተገልጿል።

በድብዳባና  በእስር ቤት  መድህኒት በመከልከላቸው ክፉኛ የታመሙት መቶ አለቃ  ተሰማ  ወንድሙ፤  ከእስር  ከተፈቱበት  እለት   ጀምሮ  ለሁለት ወር  በዘውዲቱ ሆስፒታል  ከቆዩ በኋላ በዛሬው ዕለት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

የስኳር ህመምተኛው መቶ አለቃ ተሰማ ወንድሙ በአዳሩ ሰላማዊ ሰልፍ ወቅት ከደረሰባቸው ድብደባ ባሻገር ለአምስት ቀናት ቀዝቃዛና ጨለማ ቤት ውስጥ ታስረው ቆይተዋል። የመቶ አለቃ ተሰማ ወንድሙ የቀብር ስነስርዓት ዛሬ ጥር 27/2007 ዓ.ም በቦሌ ሚካኤል እንደሚፈጸም ለማወቅ ተችሏል።

## ዘረኛው ወያኔን ከኢትዮጵያ ምድር ጠራርጎ ለማዉጣት

… ( ከገጽ 1 የዞረ )

ኢትዮጵያዊ ንቁ ተሳታፊ መሆን ይኖርበታል በማለት የተጀመረው ህዝባዊ ትግል ተፋፍሞ እንዲቀጥል ጥሪ እያቀረቡ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል። ኢትዮጵያውያኑ በተለይ በፓርቲዎች ላይ ተመርኩዘን የምናደርገው የነፃነት ትግል ለፋሽስቱ ወያኔ የተመቸ በመሆኑና ፓርቲዎች ሲጠናከሩ አገዛዙ እየጠበቀ በማፈራረስ የአገዛዝ እድሜውን ለማርዘም እየሰራ እንደሚገኝ በመጠቆም ሁሉም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በአንድነት በመነሳት በህዝባዊ ትግል አገዛዙን ለማስወገድ አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርበታል ሲሉ በመግለጽ ላይ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ለውጥ አይቀሬ በመሆኑ በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በቆየ ቁጥር የእርስ በእርስ መተላለቅና አለመረጋጋት ይመጣል የሚሉት ኢትዮጵያኑ ዲሞክራሲዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለውና የምናልማትን ነፃና ፍትሃዊ ኢትዮጵያ ለመፍጠር ህዝባዊ ትግልን ተፈፃሚ ለማድረግ በቁርጠኝነት መነሳት እንዳለብን አስገንዝበዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፋሺስቱ ወያኔ ምርጫ ቦርድ የአንድነት ፓርቲን የሰጠው ለባንዳው ትግስቱ አወሉ የተባለ ግለሰብ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ባሳለፍነው ጊዜ ተለጣፊ ቡድኑ ጠርቶት በነበረው ስብሰባ የፋሽስቱ ወያኔ አባላትን ጨምሮ በርካታ ደህንነቶች የተለጣፊው አንድነት አባል መስለው መሳተፋቸውን ለማወቅ ችለናል።

በሌላ ዜና የአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ አዲስ ምልምል ወታደሮች የኢትዮጵያ ህዝብ እየተደረገ ላለው የነፃነት ትግል ምላሽ እንዲሰጥ ጠይቀዋል። አድማጮቻችን የዚህን ዜና ዝርዝር በሐሙሱ የዜና እወጃችን ይዘን እንደምንቀርብ ከወዲሁ ለመግለጽ እንወዳለን።

**የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB  በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## 5 የአየር ሃይል የጥበቃ አባላትና 2 ፓይለቶች

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለወትሮው ይታመኑ የነበሩ የትግራይ ተወላጅ የአየር ሃይል አባላት ሳይቀሩ የሚታመኑ ሆነው ባለመገኘታቸው፣ ባለስልጣናቱ አይናቸውን የውጭ ቅጥረኞች ላይ እያዞሩ ነው።

ስርዓቱን አናገለግልም ብለው የጠፉት የአየር ሃይል አባላት የተቃዋሚ ድርጅቶችን ተቀላቅለው እየታገሉ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የአፍሪካ መሪዎችም ሆነ የሌሎች አገራት መንግስታት ለስብሰባ ወደ አዲስ አበባ በሚመጡበት ጊዜ ለደህንነት ስራም ሆነ ለልዩ ጥበቃ የሚመደቡት የአንድ ብሄር ተወላጆች ናቸው በማለት የሌሎች ክልሎች የደህንነት አባላት ቅሬታ ማሰማታቸው ታውቋል። የ24ኛው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ከተካሄደ በሁዋላ ለግምገማ ከተጠሩት ምድብተኛ የደህንነት ሰራተኞችና የጸጥታ አካላት መካከል አንዳንዶች፣ ” ለመሪዎችና ለእንግዶች ደህነነት የሚመደቡት ጠባቂዎች የአንድ አካባቢ ተወላጆች ብቻ መሆናቸው፣ “ስርአቱ የእናንተ አይደለም፣ አናምናችሁም” የሚል መልክት አለው በማለት በድፍረት ለገምጋሚዎች ተናግረዋል።

“በብሄራችን ምክንያት ተበድለናል” ያሉት የደህንነት ሰራተኞችና ጠባቂዎች፣ ደረሱብን ያሉዋቸውን በርካታ ችግሮች ዘርዝረው አቅረበዋል። ” በኢትዮጵያ ውስጥ አሸባሪዎች ራሳቸውን እያደራጁና መረባቸውን እየዘረጉ በመጡበት ሁኔታ የምናምነውን ሰው እንመድባለን” የሚል መልስ ግምገማውን ከሚመሩ መሪዎች የተሰጠ ሲሆን፣ ተሳታፊዎች በተሰጠው መልስ ማዘናቸውን በግምገማው የተሳተፉ የኢሳት ምንጮች ገልጸዋል።

## ለወያኔ ዉንብድና መልሱ ህዝባዊ እምቢተኝነትና

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

በምትካቸዉ እንደጌኛ ፈረስ የሚጋልብባቸዉን የራሱን ሁለት መናኛ ፓርቲዎች ፈጥሮ መኢአድና አንድነት ብሎ ሰይሟቸዋል። ይህ በዋና ዋናዎቹ ዘረኛ የወያኔ ባለስልጣኖች ተጠንቶ በጥንቃቄ የተወሰደዉ እርምጃ ፓርቲዎቹ ህግ ስላላከበሩ ነዉ የሚል ሽፋን ይሰጠዉ እንጂ የምርጫ ቦርዱ ሊ/መንበር ሳያስቡት ከአፋቸዉ አፈትልኮ የወጣዉ እዉነት በግልጽ እንዳስቀመጠዉ ከምርጫዉ ጨዋታ ወጥተዉ እንዲፈርሱ በተደረጉት አንድነትና መኢአድ ፓርቲና ወያኔ በተለጣፊነት ባስጠጋቸዉ ሁለቱ ተለጣፊ ፓርቲዎች መካከል ያለዉ ልዩነት አንዱ ቆሜለታለሁ ለሚለዉ ህዝብ የሚታዘዝ ህዝባዊ ሌላዉ ደግሞ ሆዱን ለሚሞላለት ወያኔ የሚታዘዝ ሆዳም መሆናቸዉ ብቻ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ወያኔ መብቴን ብለህ ስትጮህ በጥይት እየጨፈጨፈህ ነጻነት ስትለዉ በዱላ እየደበደበህና ሰላማዊ ሰልፍ ስትወጣ ደግሞ አፍሶ እያሰረህና ዉስጥ እግርህን ገልብጦ እየገረፈህ በሰላማዊ መንገድ የምታደርገዉን ትግል ምርጫ አሳጥቶሃል። ሆኖም ግልጽ በሆነ መንገድ እንነጋገር ከተባለ ወያኔ የትግል አማራጭ አያሳጣህም፤ ሊያሳጣህም አይችልም። ወያኔ እሱ እራሱ ህግ በሆነበት አገር ህጋዊ ወይም ሠላማዊ ትግል ብሎ ነገር ዋጋ ቢስ አንደሆነ ሁላችንም የተረዳን ይመስላል። ትግላችን ህዝባዊ እምቢተኝነት ነዉና ከዛሬ በኋላ ወያኔን ጥያቄ አንጠይቀዉም፤ አድርጉ የሚለንን አናደርግም፤ ሁኑ የሚለንንም አንሆንም። ትግላችን ህዝባዊ አመጽ ነዉና ከዛሬ በኋላ ወያኔ ሲገድለን እኛም እየገደልነዉ እንሞታለን እንጂ አንገታችንን ደፍተን የእሳት እራት አንሆንም። አዎ! ት ግላችን እምቢ ማለት ወይም ህዝባዊ እምቢተኝነት ነዉ፤ ትግላችን በወያኔ ላይ ማመጽ ወይም ህዝባዊ አመጽ ነዉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**